የሱር ታክስ አስተዳደር ሥርዓት

ሥልጠና

ሞጁል 8

ገቢዎች ሚ/ር

2014 ዓ.ም

ይዘት

- ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ ሁኔታ
- ክፍል ሁለት፡- የሱር ታክስ አስራር ሥርዓት
- ክፍል ሶስት፡-
- ሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት

1. መግቢያ

- የሀገር ሉአላዊነት አደጋ ላይ ሲወድቅ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሲከሰቱ፣በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኘው የኅብረተሰብ ክፍል የመንግሥትን ቀጥተኛ ድጎማ የሚፈልግበት ሁኔታ ሲከሰት… ተጨማሪ የፋይናንስ አቅም ሲያስፈልግ በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጥል ታክስ ዓይነትም ፤

መግቢያ……

መግቢያ.....

- እ.ኤ.አ.1968Lyndon B.Johnsonየቬቴናም አገር ፕረዘዳንት የነበሩ አገርቷ ለገባችበት ጦርነት ማስፈጸሚያ ለተጨማሪ ታክስ/ገቢ 10 በመቶ ሱር ታክስ ተጥለዋል፤
- በጀረምን አገርም በተለይ አገርቷ ምሥራቅና ምዕራብ ጀርመን ተብላ ለሁለት ተከፍላ ሲትተዳደር ቆይቶ ተዋሃድ አንደ አንድ አገር ሆኖ መተዳደር ሲጀምሩ ለዚሁ አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚያስፈልግ ከመደበኛ በጀት ውጭ ተጨማሪ በጀት/ወጪ በማስፈለጉ በዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ 5.5 በመቶ ሱር ታክስ
- እ.ኤ.አ. 2013ዓ.ም በተባበሩት አሜርካ መንግሥታትም (USA) በፕሬዘዳነት ኦባማ አስተዳደር ወቅት በጤና መድን አገልግሎት ላይ 0.9 በመቶ ሱር ታክስ ተጥሎ መተግበሩን መረጃዎች ያመላክታ።

መግቢያ ....

- በሀገራችንም ሱር ታክስ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ተጨማሪ ታክስ የተደነገገው በድርቅ ለተጎዱ የአገርቷ አከባቢዎች ማቋቋሚያ እና የተፈጥሮ አደጋን ለመከላከያ የሚውል ገንዘብ እንዲገኝ በገቢላይ ጊዜያዊ ተጨማሪ ታክስ ለመወሰን መጋቢት 2/1967 ዓ.ም በወጣው አዋጅ ቁ. 24/1967 ነበር፡፡
- በሚኒስተሮች ምክር ቤት በተደነገገው ደንብ ቁጥር 133/1999 መሠረት በዚሁ ደንብ ነጻ ከተደረጉት በስተቀር ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ እቃዎች ላይ 10% ተጨማሪ ቀረጥ (ሱር ታክስ) እየተጣለ እየተሰበሰበ ይገኛል፡፡

ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ

1.1. ዋና ዓላማ

በተጨማሪ ቀረጥ ወይም ሱር ታክስ የህግ ማዕቀፍና አሠራር ሥርዓት ላይ ደንበኞች በታክሱ ዙሪያ መብታቸውን በማስከበር ግዴታቸውን እንዲወጡ ግንዘቤ ለማስጨበጥ ነው

ዝርዝር ዓላማዎች

ሠልጣኞች፡-

- የሱር ታክስን ምንነት ይገልጻሉ ።
- ከሱር ታክስ ነጻ የሆኑትን ገቢ ዕቃዎች/ግብይቶች ይለያሉ።
- የሱር ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶችን ይገለጻሉ።
- የሱር ታክስ የስሌት መሠረት ይረዳሉ።
- ሱር ታክስን ያሰላሉ።

1.2. ወሰን

1.2.1. ሽፋን

የሱር ታክስ አስተዳደርን አስመልክቶ ስለተደነገገው ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተጨማሪ ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 133/1999 ዓ.ም እና በተለያዩ ጊዜያት የተላለፉ ሰርኩላሮች;

ወሰን........

1.2.2. የሥልጠናው ተሳታፊዎች ዕቃዎችን ወደ አገር በማስገባት በንግድዓለም የተሰማሩ ድርጅቶች/ግብር ከፋዮች፤

1.2.3. ሥልጠናው የሚወስደው ጊዜ



ክፍል 2

2. የሱር ታክስ አስራር ሥርዓት

2.1. ሱር ታክስ ምንድን ነው **?**

- መንግሥት ሜጋ ፕሮግራሞችን እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ የልማትፕሮጀክቶች/አገልግሎቶችን በመደበኛ በጀት/ፋይናንስ ፍሰት ወጪዎችን ለመሸፈን እንዲችልና የበጀት ጉድለትን ለማሟላት በዕቃዎ/አገልግሎቶች የሚጣል ተጨማሪ ታክስ
- በደንብ ቁጥር 133/1999 በተደነገገው መሠረት በዚሁ ደንብ ነጻ ከተደረጉት በስተቀር ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ 10% ተጨማሪ ቀረጥ/ታክስ

2.2. የታክሱ ስሌት መሠረት

- የዕቃው ዋጋ፣ የመድን አረቦን እና የማስጫኛ ወጪ (Cost, Insurance and freight) እና
- በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የኤክሣይዝ ታክስ ድምር ይሆናል።

ሱር ታክስ ስሌት.....

- የተሽከርካሪው ዋጋ =240000 ብር የማጓጓዣ ዋጋ =50000 ብር ኢንሹራንስ ዋጋ =1000 ብር የጉምሩክ ቀረጥ ምጣኔ =35% የኤክሳይስ ታክስ ምጣኔ =60% ሱር ታክስ 10% ቢሆን ቀረጥና የታክስ ስሌቱ እንደሚከተለው ይሆናል
- የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ=C+I+F

  =240000+50000+1000=291000 ብር

ሱር ታክስ ስሌት .....

ተ.ቁ	የታክስ ዓይነት	የታክሱ መሰረት	የታክሱ መጣኔ	ታክስ
1	የጉምሩክ ቀረጥ	291000	35%	101850
2	የኤክሳይስ ታክስ	291000 +101850	60%	235710
3	የተ.እ.ታክስ	291000 +101850+235710	15%	94284
4	ሱር ታክስ	**291000 +101850+23**	**10%**	**72284**

2.3. ከተጨማሪ ቀረጥ (ሱር ታክስ) ነጻ ስለመሆን

- ታክሱ የማይመለከታቸው /ከታክሱ ነጻ የሆኑ እቃዎች/ ግብይቶች
- የመሬት ማዳበሪያዎች፣
- ነዳጅ፣ የብረታ ብረት ቅባቶች፣
- የጭነትና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች እና ለተለየ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች፣
- አውሮፕላኖች፣ የአየርና ጠፈር መንኮራኩሮች፣ እና የነዚሁ ክፍሎች፣
- የካፒታል (የኢንቨስትመንት) ዕቃዎች
- በሕግ ወይም መንግሥት ባደረገው ስምምነት ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የተደረጉ ሰዎች እና ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች ናቸው ።

ስሌት ...

ማጠቃለያ

- ተጨማሪ ታክስ (ሱር ታክስ) የሚባለው አንድ የተወሰነ ፕሮግራምን ፋይናንስ ለማድረግ ሲሆን በመደበኛነት የሚሰበሰቡ ታክሶች ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ወጪዎች ይሆናል።
- ታክሱ መንግስት ለአንድ ለምን ዓይነት የተወሰነ አገልግሎት ምን ያህል ወጪ እንደተደረገ ታክስ ከፋዮች እንዲያውቁት ማድረግ የታክሱ ልዩ ባህርይ ነው።

ማጣቃሻ

- በሚኒስተሮች ምክር ቤት በተደነገገው ደንብ ቁጥር 133/1999

ሱር ታክስ …

- የሙከራ ጥያቄዎች

1. የሱር ታክስን ምንድነው ?
2. ከሱር ታክስ ነጻ የሆኑትን ገቢ ዕቃዎች/ግብይቶች ለዩ፤
3. የሱር ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶችን ግለጹ፤
4. የሱር ታክስ የስሌት መሠረት ጥቀስ፤
5. ሱር ታክስን ስሌትን በምሳሌ አስረዳ፤

አመሰግናለሁ!

Email: morethiopia@gmail.com